የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

ቀን ግንቦት 0 2 2010
Date
ቁጥር 0030-835/3
Ref. No.

በናይሮቢ የምትገኙ በዓለም አቀፍ ድርጅት ውስጥ የምትሰሩ ወገኖቼ
<u>ናይሮቢ</u>

ከሁሉ አስቀድሜ ሚያዝያ 28 እና 29 ቀን 2010 በናይሮቢ ከተማ ባደረግሁት ጉብኝት ላደረጋችሁልኝ ደማቅ አቀባበል፣ በቆይታዬ ጊዜ ላሳያችሁኝ ፍቅር እና አርባ አንድ (41) ሆናችሁ በመፈረም ለሰጣችሁኝ የመልካም ምኞች መግለጫ እና በደብዳቤያችሁ ላይም የያዝነውን የለውጥ ጉዞ ከልባችሁ የምትደግፉና በተሰማራችሁበት ሙያ ሁሉ አገራችንን ለማገልገል ቃል መግባታችሁ ከልብ ያስደሰተኝ መሆኔን ልገልጽላችሁ እወዳለሁ::

አምባሳደር ሳህለወርቅ ዘውዴ በናይሮቢ የተባበሩት መንግስታት Director-General (Under-Secretary-General Level) ወገኖቼን በማስተባበር United Nations Environment Programme (UNEP) እና United Nations Human Settlements Programme (UN-Habitat) በሚገኙበት በደን በተዋበ ግቢ ውስጥ ችግኝ እንድተክል እና በመጨረሻም ከወገኖቼ ጋር እንድተዋወቅ ስላደረጉኝ ከልብ አመሰግናለሁ::

ስለዚህ ውድ ወገኖቼ እናንተም ሆናችሁ ሌሎች በአቅረቢያችሁ የሚገኙ ወገኖቼ አገራችን ከመቼውም በላይ የእናንተን ድጋፍ ስለምትፈልግ በሙያችሁም ሆነ በገንዘባችሁ ልባችሁ ያሳሰባችሁን በማድረግ አገራችሁን እና ወገናችሁን እንድትረዱ ጥሪዬን አቀርብላችኋለሁ::

ከሠላምታ ጋር

ዐቢይ አህመድ (ፒ.ኤች.ዲ.)
ጠቅላይ ሚኒስትር

ስልክ 011-1-22-67-67 Tel.
ፋክስ 22 62 92 Fax
ፖ.ሣ.ቁ 1268 P.O.Box
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa-Ethiopia